# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 3 ልዩ ዕትም 1 ጥቅምት ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ.ም.


## አያ አስማማው! ብዕርህ ይናገር

*(የአቶ አስማማው ኃይሉ ዜና ዕረፍት ምክንያት በማድረግ)*

ቡና ሀገር ልገባ ገዳሪፍ መጥቼ
የሚያለማ መስሎኝ በሰው ተሳስቼ
ባክኜ ቀረሁኝ ካገሬ ወጥቼ።
ማሪኝ ወርቅ አፈራው ጋሜ ባለቤቴ
ያለ ጧሪ ቀረ ሽማግሌው አባቴ
ማየት የተሳነሽ አሮጊቷ እናቴ
እኔስ መቼ ቀናኝ አሜርካ ኑሮ
ነጋ መሸ በቢል ልቤ ተሸብሮ።




ሰፈ ጎጆ አዳራሽ ጌታ የሌለበት
የወንዛችን ውኃ ቢል ማይመጣበት
ቢሰበር መካኒክ ጋራ የማይሻው
ቡላው አህያችን ጭነት የማይገታው
እንደ ዋዛ ቀረ ችምችም ያለው መንደር
አሁን ቢቸግር ነው እንጂ ኒዎርክ ነው ወይ ሀገር።

**"ይድረስ ለአያ ሻረው" በሚለው ግጥሙ የሚታወቀው አቶ አስማማው ኃይሉ ረቡዕ ጥቅምት 04 ቀን 2008 ዓ.ም. (October 14, 2015) ማለዳ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።**

***"ዘመን የተጋራኝ ትውልድ ያገሩን ሥርዓት ወደ ተሻለ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ይዞታ ለማሸጋገር አልሞ በአያሌ የሕይወት ውጣ ውረዶች አልፏል። ሞትንም ጨምሮ። ከሞትና ከእስር ያመለጡት ደግሞ ባገኙት አጋጣሚ ሀገራቸውን እየጣሉ ተሰደው ከአዲስ ኑሮና ባህል ጋር ለመመሳሰል ፈተናዎችን ተጋፍጠዋል። ሕይወት በኑሮ ድግምግሞሽ ይለመዳል። የተሰበረ ስነ ልቦና ግን ገጠመኞችን እየተመረኰዘ አመጣጥን ይዘክሩ ዘንድ ሕሊናን መወትወቱ አይቀርምና በዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ጫና ያሳድራል።" አስማማው ኃይሉ፦ ከደንቢያ - ጎንደር እስከ ዋሽንግተን ዲሲ ታሪካዊ ልብወለድ, 2002 ዓ.ም.***

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢ.ሕአሠ) አባል የነበረው አስማማው ኃይሉ በአሲምባ በፖለቲካ ትምህርት የተካፈለና የኃይል 500 አባል ሲሆን ሠራዊቱ ከአሲምባ ካፈገፈገ በኋላም በበለሳና አርማጮህ ወታደራዊ ግዳጁን ተወጥቷል።

አቶ አስማማው በ2003 ዓ.ም እና በ2006 ዓ.ም. ኢ.ሕአሠ ቅጽ 1 እና ቅጽ 2 እውነተኛ የኢ.ሕአፓ ሠራዊት ታሪክ እንደ ቅደም ተከተላቸው የፃፈና ለንባብ ያበቃ ነው።

የመጀመሪያውን ቅጽ የኢ.ሕአሠ ታሪክ መጽሐፍ በመግቢያው ላይ እንደገለጸው መጽሐፉ የሚያተኩረው በኢ.ሕአሠ ታሪክ ውስጥ ጎልተው በታዩ አጠቃላይ ኩነቶች ላይ እንደሆነ ይነግረናል። የኢ.ሕአፓ ሠራዊት በተንቀሳቀሰባቸው አካባቢዎች ዙሪያ ከሚኖሩ ሕዝቦች ጋር ስለነበረው ግንኙነት፣ በመሪው ፓርቲ ኢ.ሕአፓና በሠራዊቱ መካከል የነበረው የአሠራር ዘይቤ አዎንታዊና አሉታዊ አንደምታ፣ በሠራዊቱና በፓርቲው አመራር መካከል ተፈጥረው የነበሩ አለመግባባቶች፣ እና ሌላም በሰፊው ሊፃፍባቸው ቢችሉም ደራሲው የራሱን አበርክቶ አስነብቦናል። ስለ መጽሐፉ ሲገልጽ “ትናንትናንና ዛሬን የምንቃኝበት መነጽር ነውና ትምህርታዊነቱ አጠያያቂ አይደለም።” ይለዋል። ቀጠል በማድረግም “በኢ.ሕአፓ/ኢ.ሕአሠ ታሪክ ዙሪያ የሚቀርቡ መጣጥፎች ሁሉ ለታሪክ የሚቀሩ መረጃዎችን እንደሚያበረክቱ አልጠራጠርም።” ሲል አጠንክሮ ይገልጸዋል።

እርግጥ ዛሬ አቶ አስማማው በሕይወት የለም። ወደድንም ጠላን ኢ.ሕአፓ/ኢ.ሕአሠን በተመለከተ ዳቦስ ያለ መረጃ ትቶልን ያለፈ ዋነኛ ሰው ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ የስነ ጽሁፍና የቋንቋ ችሎታውን ቀደም ሲል በፃፈልን “ይድረስ ለአያ ሻረው” ግጥሙና “ከደንቢያ-ጎንደር እስከ ዋሽንግተን” መጽሐፉ ያስመሰከረ ወገናችን ነው።

አቶ አስማማው በቅጽ 1 የኢ.ሕአሠ ታሪክ ከ1964 እስከ 1970 ዓ.ም. ያለውን በአብዛኛው በወቅቱ በነበሩና በአገኛቸው መረጃዎች ተደግፎ ያቀረበልን ሲሆን የአፃፃፍ ስልቱም የራሱን አስተያየት እምብዛም ሳያክልበት በሕይወት ያሉና በተለያየ ጉዳይ ያናገራቸውን፣ ያወያያቸውን የሠራዊቱ አመራር አካላትና አባላትን ቃል እንዳለ በማስቀመጥ ነበር።

ከ1970 እስከ 1972 ዓ.ም. ያለውን የኢ.ሕአሠ ታሪክ የራሱን ግንዛቤ በማከል በቅጽ ሁለት መጽሐፉ አስነብቧል። መጽሐፉ የኢ.ሕአሠ ክፍል አንድ መጽሐፍ ቀጣይ ታሪክ ነው። እንደ ደራሲው አባባል የመጽሐፉ ታሪክ የሚያጠቃልለው ኤርትራ ውስጥ ለስድስት ወራት በጥገኝነት የቆየው የአሲምባው ሠራዊት ቤጌምድር ከሚገኘው የኢ.ሕአሠ ሠራዊት ጋር ከተቀላቀለ ከመስከረም 1971 ዓ.ም. ጀምሮ ብተና እስከተካሄደበት ሰኔ ወር 1972 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ያለውን የትግል ጊዜ ነው። ሠራዊቱ በአራት ሪጅን ተዋቅሮ የተከናወኑትን ወታደራዊና ፖለቲካዊ ተግባራት ዘርዘር ባለ መልኩ ደራሲ አስማማው ኃይሉ አቅርቦታል።

“በኢ.ሕአፓ/ኢ.ሕአሠ የትግል መስክ የተሳተፉና የተሳታፊዎች ቤተሰቦች በዚህ ድርጅት የመጨረሻ ዕጣ እስከ ዛሬ ግራ እንደ ተጋቡ በየማሕበራዊ ስብስቦች ተዘውትረው ይነሳሉ” የሚለው አያ ሻረው “ትግሉ የጠየቀውን መሪር መስዋዕትነት በከፈሉና በቀሪዎች ሕሊና ላይ ጥሎት ባለፈው ጉዳትም ፀፀትንና ቁርሾዎችን ብቻ የሚያስተናግድ የታሪክ ክፍል ሆኖ ቀርቷል። ይህ ደግሞ የኢ.ሕአፓ ትግል መርሕ ለታሪክ ጥሎት ያለፈውን ድርጅታዊ ትግል ተመክሮ፣ ለመደብና ለብሔር ነጻነት መነሳትንና የዓላማ ጽናት እሴቶች ዋጋ ሊያሳጣ አይገባም። ታጋዮቹ ለሀገርና ለሕዝብ የተሻለ ሕይወት በጀግንነት ተዋድቀዋል። ከዚህም አንጻር ፓርቲው በመጨረሻ ከአረፈበት ዕጣ በመንደርደር ለተከፈለው መስዋዕትነት ዋጋ መንሳት ትክክል አይደለም። ተወደደም ተጠላ አሁን በሀገራችን ላለው ሥርዓት ሕልውና

የዚህ ድርጅት አባላት አስከሬን ዛሬ በምንራመድባቸው ጎዳናዎች ላይ ቀኑን ሙሉ ተሰጥቶ ስለመዋሉ ሕዝብ ይመሰክራልና!!” በማለት የመጽሐፉን መግቢያ “መልካም ንባብ” ብሎ ይቋጨዋል።

አቶ አስማማው (ኢያ ሻረው) ለሀገርና ለሕዝብ ያበረከታቸው መጽሐፍት ምንጊዜም ሕያው ያደርጉታል። መጽሐፉ የራሱ የሆኑ ጉድለቶች አሉት ባዮች ቢኖሩም በአገኘው መረጃና በሚያውቀው መጠን ለትውልድ አንድ መረጃ አስተላልፏል። ስለ አሲምባና ኢሕአሠ ታሪክ የመጀመሪያው ፀሐፊ ያሰኘዋል።

ዛሬ ኢያ ሻረውን የምናነጋግረው “ይድረስ ለኢያ ሻረው” በሚለው ግጥሙ ውስጥ ነው። የኢያ ሻረው የስደት ሕይወት ታሪኩን የሚያውቁ ወዳጆቹና ቤተሰቡ አስማማውን የሚያዩት “ከደንቢያ-ጎንደር እስከ ዋሽንግተን ዲሲ” በሚለው ታሪካዊ ልብወለድ መጽሐፍት ውስጥ ነው። የኢሕአፓ/ኢሕአሠ ታጋዮችና የትግል ጓዶቹ ስለ ኢሕአሠ በጻፋቸው ሁለት መጽሐፍት ውስጥ ከኢያ ሻረው ጋር ይነጋገራሉ። አቶ አስማማው ከመቃብር በላይ ስሙን ተክሎ ያለፈ ኢሕአፓ/ኢሕአሠ ያፈራው የያ ትውልድ ወገን ነው።

በራሱ አንደበት ያነበበው ወደ ሁለት ሰዓት የሚፈጀው የአስማማው ኃይሉ “ይድረስ ለኢያ ሻረው” ግጥም የአሜሪካንን የስደት ሕይወት በጣፋጭ የአማርኛ ቅላጼ ተርኮልናል። ግጥሞቹን ለማድመጥ (http://yatewlid.com/mp3/AyaSharew%201.mp3 እና http://yatewlid.com/mp3/Ayasharew%202.mp3) ይጠቀሙ።

እያዝናና፣ እያሳቀ፣ እያስገረመ፣ እያስቆዘመ፣ ሀገረ አሜሪካንንና ገጠሪቷን ኢትዮጵያ በዓይነ ሕሊናችን ይስልብናል። ኩሩ ባህላችን ናፈቀኝ እያለ ያዜማል። ያለ መግባባቱን የቋንቋ ችግሩን በደንብ ይነግረናል። ሀገሬ ኢትዮጵያ እያለ በውስጡ ይዘምራል። ወንዙ፣ ሸንተረሩን፣ የከብቶቹን ጩኸት ይጮሃል። ባህሌ ክብሬ፣ እኔስ ኮራው በሀገሬ ይለናል።

“ቺዝ በርገር፣ ፍራይዝ፣ ችክን
አቤት የምግባቸው ብዛት እያለ ይስለዋል፡ የበላው ትዝ ሲለው ይሰቀጥጠዋል

“ምን ያልተበላ አለ ከዚህ ድርቡሽ ሀገር
ለቄስ ካልተጠመኩ ተመልሼ ካገር ። ብሎ ይናዘዛል።

ስለ ሴት፣ ስለ መኪናው ብዛት፣ ስለ መንገድ ሥራቸው አንዱም አልቀረውም ኢያ ሻረው።

“በመሬት መንቀጥቀጥ ሕዝብ አለቀ ብለው
ነገሩ ሳይገባኝ ወዲያው ቀጠል አርገው
ይሉሃል መቶ ቤት እሳት አቃጠለው።
ለሰዉ ሕይወት መጥፋት ትንሽ የማይባቡ
ለንብረት መጥፋት ነው የሚንገበገቡ። እያለ የቴሌቪዥኑን ዲስኩር ይተርካል።

“ጎረቤት የሚባል ከዚህ ሀገር የለም
ለዘመድም መሞት ሀኅበር አይጥሉም
ለትኩስ ሬሳም በወግ አያለቅሱም
እንደኛው ሀገር ሠርግ እንደ ክርስትናው
ለሞተም ሰው ቢሆን መግለጫ አበባ ነው

አይ ወንድሜ ማለት፣ አይ አኅቴ ማለት ከቶ አይሞክሯትም። በማለት የአሜሪካንን ሀዘንተኛ ከሀገራችን ያነጻጽረዋል።

ከሀገራችን አዝመራ ጋር የመኪናውን ብዛት ሲያዛምደው

“አቤት የመኪና ብዛት ትርምስምስ ትርምስምስ
ንፋስ እንደነካው እንደ በልግ እሸት ገብስ። እያለ አገላለጹን ውበት ይሰጠዋል።

“ይኸውልህ ድፍን የኢትዮጵያ ልጅ ሀገር እንደሌለው
ሲቻት እንደጥጡ ሲባዘት መኖር ነው
የሰው ልጅ ክብሩን ፍጹም እረስቶታል
ድመትና ውሻ ወጉን ቀምቶታል
አያ ሻረው! ሀገር አይመስልህ ሁሉም ግርምቢጥ ነው
ከሰው ልጅ በበላይ በጣም ተከባሪው ውሻና ድመት ነው።

በማለት ኢትዮጵያዊነት ኩራታችንን፣ ክብራችንን በስደት ማስረከባችንን ይነግረናል።

“ድሮ ተኛ መንደር ከከተማው መጥተው ሳይቀሩ በሙሉ
ጓድ፣ ጓድህስ፣ ትግልስ፣ ነጻነትስ፣ ምንትስ፣ አንዳችስ የሚሉ
እንደ ቅቤቱ ቅል በጣም ወዝ አግብተው እዚህ ሀገር አሉ።
ከእርሻው መሃል ጠርተው ሲሉኝ እንዳልነበር ሰላም ሃያ ጓዱ
ሃይ! ያቸውም ቀርቷል ገፍተውኝ ማለፍ ነው ሲያዩኝ በመንገዱ
ፍቅራቸው የጠና የቃልኪዳን ነበር የሚመስለኝ ድሮ
አይ ሰው ፈራሹ ማተብ አንገት የለው ትንሽ አያይ ዞሮ
የልብ ያንጀት ሰዎች እየገቡ አለቁ
ትንሽ ተግ ያሉትም ይኸው ወዙን አልፈው እዚሁ ዘለቁ
እነቀን አያውቁ…. ሳይጠይቁ እየገቡ አለቁ። በሚል ቁጭት ስደት የቁም ሞት መሆኑን እያዋዛ ይነግረናል።

አያ ሻረው የሰው ናፍቆቱን እንዲህ ሲል ይገልፀዋል

“እህል ውኃ መሳይ ፍቅር ያለበት ሰው
አመንዥኮ እንዲሞት ሀገሩ ተዚህ ነው
ሻኛ እሚያሳብጥ ወርች ሚያወፍረው
ምግብ እንዳይመስልህ ናፍቆት ሲረካ ነው።
ይኸውልህ ወገን ሰርክ ለት ሚጨንቀኝ ከልቤ የማዝነው
ብል እንደበላው ጨርቅ የምብተከተከው
በጣፍኩልህ ቁጥር ቅሬታ ምገልጠው
ጨርቅ ምግብ ሞልቶ ሰው ግን ቸግሮኝ ነው።

አቶ አስማማው ብዕሩ ነጥፏል፣ ልሳኑ ተዘግቷል። ከእንግዲህ ለህትመት ሰጥቶት ያሸለበው የመጨረሻ መጽሐፉ ለንባብ በቅቶ ከማንበብ በቀር ሌላ አናገኝም። ግና ትቶት ያለፈው ሥራው ገና ብዙ ይሰራበታል፣ ይፃፍበታል። ሥራዎቹ ለሌሎች ተዛማጅነት ላላቸው ሥራዎች ማጣቀሻነቱ አጠራጣሪ አይሆንም። ለምርምርና ለጥናት ሥራ ከየቤተ መጽሐፍቱ ይፈለጋሉ። ስለ ኢሕአፓ/ኢሕአሠ የሚጽፉ፣ የሚያጠኑ፣ የሚመራመሩ ሁሌም ከአስማማው ኃይሉ ጋር ይነጋገራሉ። ከመጽሐፉ ለጥያቄዎች መልስ ይፈልጋሉ፣ መጽሐፎቹ ሌላ ጥያቄ ያስነሳሉ፣ ብዙ እንዲፃፍ ይጋብዛሉ። አስማማው የችሎታውንና የድርሻውን የትውልድ ግዴታውን ተወጥቷል ማለት ይቻላል። አንደበቱን፣ አካሉን፣ ማንነቱን በመጽሐፍቱ አስቀምጦልን አልፏል።

«ያ ትውልድ ተቋም» በአቶ አስማማው (አያ ሻረው) ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን ለመግለጽ እንወዳለን። አቶ አስማማው «ያ ትውልድ ተቋም» እየሠራ ላለው የመረጃ ማሰባሰብና የተሰዉ ወገኖቻችን መታሰቢያ ድረ ገጽ በማድነቅ ሊደረግ የሚችለውን ትብብርና ድጋፍ ሲያደርግ የነበረ ወገናችን ነበር። የኢሕአሠ እውነተኛ ታሪክ መጽሐፉን ቅጽ 2 ለ«ያ ትውልድ ተቋም» የማሳተምና ማከፋፈል ሀላፊነቱን በመስጠት የመጀመሪያው ሰው ነው።

አያ ሻረው ዛሬ ሩጫውን ጨርሷል። አምስት ጣቶቹ አፈር ጨብጠዋል። ኢትዮጵያ አንድ ልጇን አጥታለች። ያ ትውልድ አንድ ወገኑን አጥቷል። በሕይወት ዘመኑ ጥሎልን ያለፈው ሥራዎቹ ለአሁኑና ለመጭው ትውልድ በክብር ይተላለፋሉ። ጊዜ የማይሽረው መጽሐፍቱ ምን ጊዜም ተነባቢ ናቸውና ስሙ ከመቃብር በላይ ሁሌም ይነሳል። ትውልድ ሁሉ ያነቡሃል። የዜማ ቅላጼህን ያደምጡታል። አኩሪ ተግባር ፈጽመህ በማለፍህ ሞትህ እረፍት ነው።

በመጨረሻም በዛሬው ዕለት የሚፈፀመውን የአቶ አስማማው ኃይሉ የፀሎትና የቀብር ሥነ ስርዓት ምክንያት በማድረግ «ያ ትውልድ ተቋም» በአባላቱ ስም ለአቶ አስማማው ኃይሉ (አያ ሻረው) ቤተሰብ፣ ዘመድ አዝማድና ወዳጅ ጓደኞቹና አድናቂዎቹ በሙሉ ሀዘናችሁ ሀዘናችን ነውና ሕግዚሃብሔር መጽናናቱን ይስጣችሁ እንላለን ከ «ያ ትውልድ ተቋም»።

ከአቶ አስማማው ግጥም "ይድረስ ለአያ ሻረው" ስለ እምዬ ኢትዮጵያ ያለውን ጨለፍ አርገን እንደራሱ አባባል እናቀርባለን። ይህን ግጥም በገጣሚው አንደበት ለማድመጥ እዚህ ይጠቁሙ

http://yatewlid.com/mp3/AyaSharew_Clip.mp3



"…ታዲያ ይኸውልህ የአበሻው ብዛት በዚያ ቀን የዋለው
ቁጥሩን አላውቀውም ዝም ብሎ ዘሊብ ነው
ዓይኔ ቆቡ ደክሞ ወድቆ እስከ ሚጨልም
ብታዘብ ብማትር በኢትዮጵያ ሀገራችን
ባድማ ጠባቂ ሰው የቀረ አይመስልም።
ሰዓት ተጠብቆ ንግግር ጀምረው
መደስኮር…መደስኮር…ወግ አያልቅባቸው
ብዙ የባድ ቋንቋ ደብልቀው ቢያወሩም
ኢትዮጵያ ለሚለው ቅያሬ አላገኙም
እንደየንግግር እንዳሳብ ዘይቤሃቸው
ተግ! ግንፍል! የሚያደርግ ባህሪም አላቸው።
አንዱ ጥርሱን ነቅሶ ጣቱን ቀስሮ አያል ቃል ሲናገር
ሌላኛው ቀጥሎ አፍ አፉን ይለዋል በሽሙጥ በነገር
እጅ ባይጠመዝዝ ባትጠልፈው፣ ባይጥልህ
ዲስኩር ፖለቲካ ማለቂያም የለውም።
አንዱ አላቢላ ተምሬአለው የሚል
እኔን ትምህርት ያርገኝ
ጅል ንግግር አርጐ እጅጉን አስቆጣኝ።
ያ ቅርሻታም አፉን ክፉኛ አሞጥሙጦ
አንዳች ሠይጣን መሳይ መጽሐፍ ገልብጦ
"ኢትዮጵያ የምትሏት ይቺ የናንተ ዓለም
ስሟ የዛሬ እንጂ አልዋለም አላደረም
አያልናት ብላችሁ ብትዘፍኑም ዘላለም
ማሽብሸብ ነው እንጂ
ከመቶ ዓመት በላይ ምንም ታሪክ የለም"
አይልም መሰሎሃል አንድ ሆፔ የነፋው
በጣይ መብረቅ ጥሎ ገልብጦ እንዳይደፋው።
ኸረ ባ.ዛ.ኝ.ቱ.! ዓይነን አርገብግቦ ጆሮ ያሳከከኝ
ይህን ጉድ ሊያሰማ አንሰፍስፎ አመጣኝ።
ከዚያ በኋላማ የመነጋገሪያ ህጋቸውን ጥሼ

ያንን ሃሳዊ መሲ ላቀምሰው ደርሼ
ምስ ምሱን ነግሬው
ቡጢ ከፈለገም ባፍጢሙ ልደፋው
አቦ ይወቅብኝ ይህን ፈርሳም ባምባ ከጉዳይ ጥፌው ነው።
አንት ውፉራሽ ሌባ፣ አንት ተሻይ ቤት አደር
ታሪክ እንደ ጁባ እንደ ጨው ምትቀይር
በሀሰት መስካሪ ላበላህ ትራፊ
መሠረተ ወግ የለሽ አዲስ ታሪክ ጣፊ
እስቲካ ልንገርህ ተቀበለኝ ስማኝ
አስኳላስ መዳኒት አንተው መንደር ተርፎ ለኔ ማን አቅምሶኝ
ካርኒ ቆራጭ ልኮ መንደራችን ያየው
መንግስት ገንዘብ ሲሻ አስራት ሲያስከፍል ነው
ደረቅ ጡቷን ጎርሰህ በቁምህ ልገኸው
ዛሬ ተገልብጠህ ስሟን ስታረክሰው
እኔ ያንተን ያህል ምኑን አግኝቼው ነው
ባባት አደራ እንጂ ቁም ስቅሌን ማየው
አንተ ባታውቃቸው እኔ እንዴት እረሳ
ባርማጮሆ ጠለምት በቋራ በለሳ
መቼ ዘር መለያ ምልክት አላቸው
በፋሽስት ጥይት ያለፈ ነብሳቸው።
ባንዲራ ቀይ ነው በተክሲያን ባይስሙም
ውሸት ምን ያደርጋል ስለ ኢትዮጵያማ አውርተው አጠግቡም
ተምን እንደሆነ ሳናውቀው ዘራቸው
ዝርያ አበቃቀል አውድማ ጎጣቸው
እኛ ሞረሽ ብለን ሰው እንደምንጠራው
የነሱም መጠሪያ ጓድና ጓዲት ነው።
አሁንም የሆነ እንደሆነ ምነው አላወራው
ከጥንትስ ጠቅሼ
ተራ ገጡም ሳይዘል መሠረቱን ይዤ
በካሣ ደም በቅሎ ዘሩ የምናየው
የጋራ ነው እንጂ ብንተወው ብንበላው
የኢትዮጵያ እህል እንጂ ጐንደሬነት አለው?
አጤ ዮሐንስስ ማሰሪያውን ያጡ ማተብ አጠብቅ ብለው
ለሀገር ብለው እንጂ ለወርቅ ለንዋይ ነው?
ከዚያ በኋላሳ ያጤ ምንሊክ ጦር አድዋ የቀረው
ለነጽሳነት እንጂ እርስት ሊያቀና ነው?
አንተ አጐዛ ብጤ አረም አረማሞ
ነግሬህ አርፍ እንጂ አይቀር ሆዴ ታሞ
ሱሪ ተፈታታኝ ህግ ተገን አድርገህ
እንዴት በሀገሬ ላይ እጅጉን አላገጥህ?
መደበቂያ የለ ቃታ አይሳብ ነገር
አይበቀል ብያ ሆነና ባድ ሀገር
ዕብድ አንጎል አድርጎኝ አስቶኝ ነበረ
ታዲያ ምን ያደርጋል ምስክር በዛና ሁሉም ሳይሆን ቀረ
አልዋጥ ብሎልኝ ካንጀት ሆድ ቢብሰኝ
ዲስኩር ስብሰባውን ትቼላቸው ሄድኩኝ።
የዚያ ቀን ክፉቱ ምን ምህረት አለው
ንጉሥ ሀገር ጥለው ሽምጥ መጥፉታቸው
የዕለቱ ስብሰባ ወሬ ነው ያመጣው




ብዬህ እንጂ ነበር ጋሻዬ ባትሰማም
ጓድ ብሎ ንጉሥ ብዙ ዕድሜም አይገፋም
እንዲያ በራዲዮን አያል ዲስኩራቸው
አንድ ሰው እስኪቀር የሚለው ጉራቸው
ምነው ሰው ሁሉ አልቆ ሳይለይለት ውሉ
በውሮፕላ ቀድመው ከሀገር ኮበለሉ።
አንገት አስደፍቶ የሚያሳፍር ሀገር
እኔ እያለሁ ብሎ መፈርጠጥ ጅል ነገር
ጥንተ ነገሩማ ያልገጠመ ውሉ
በጣምራስ ሄደው ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ደፍረው ተማሰሉ
ጥቃት ድንገት ደርሶ ሲተናነቃቸው
የየቅል ሆነ አጨራረሳቸው።
እኮ እንዴት? ብትላ
እኛ በራስ መፍረድ እኚህ በውሩፕላ
መጥኔ…
እሳቸውም እኔ ሀገሩን ልንተወው
ቧምቧም ሆነና እሳት ሚተፉ አልከው
ሰው ከውሮፕላ ሲያምሱን የኖሩ
ምኑን እጥፍ አንጀት አረዛ ነበሩ
ስማኝ መድሃኔዓለም ጥንት ምዘክርህ
ያ ሁሉ ደም ሲፈስ በትዝብት ዓይን አይተህ
ፍርዱን በሮጡበት ካልመዘንከውማ
ሥራህ ግርምቢጥ ነው ያው እንዳሜሪካ።
ወንድም አያ ሻረው!
ይህ አዲሱ መንግሥት ተራገጥ ወረዱ
ምንድን ይመስልሃል የግዛት መንገዱ?
ቁሙ ተጠበሱ ታመሱ የሚል ነው?
አረንጓዴ ቢጫ ቀዩ ባንዲራችን እሚል ዘፈን አለው?
በጣም ተባበሩ አንድ ላይ ሆናችሁ
ሰላም ጠሎት ስጡ ለኢትዮጵያ ሀገራችሁ
ዘርና ወገሻ ማጥበቁን ትታችሁ
የሚል ቃል ወጥቶታል?
እንዲህ ካሰበማ አረጋገጥ ያውቃል
አለበለዚያ ደግሞ ካዳሙ ሕዝብ ጋር ትኩር ጥምድ አርጎት
በልቡ አሳድሮ ጥርጣሬ ስጋት
ጠመንጃ አስረክቡ ትጥቅ ፍቱ ካለ
ባላገርን ንቆ እራስ ከሄደና ትንሽ ከቀለለ
ዘመቻ ቢያበዛ ቢያቃጥል ቢያርስ ምድር
አደራ እንዳትፈቱ አባ ታጠቅ ዝናር።
አያ ሻረው
ጅብ እንደ ሀገሩ ይጮሃል እንዲሉ
አልጥምህ እያለኝ ኑሮው ዘዴው ሁሉ
ከዚህ ከአሜሪካን የንወርክ ኑሮዬ
ከተውኩት አይገኝ ልክ እንደ ጥላዬ
ዛሬ የለመድኩት ነገ እያረጀብኝ
መከተል መቀየር በጣሙን ሰለቸኝ።
በል እንግዲህ!
ሀገር ሰላም ይሁን ይቃና መንገዱ
ልጅ ሙላለም ከኒዎርክ ሰላም ብኋል ብለህ ንገር ለዘመዱ።

**ጥቅምት ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ.ም**. (October 24, 2015)

**<u>«ያ ትውልድ ተቋም»</u>**

**ድረ ገጽ** ፡ www.yatewlid.org, www.yatewlid.com
**ኢ.ሜል** ፡ yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com